የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

HOUSE OF PEOPLES'REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት

# የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

# የ2014 ዓ.ም የ3 ወር /ከህዳር እስከ ጥር/ ሪፖርት

## ድርሞ /Executive summary /

የቀድሞው የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃት የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚል ተደራጅቷል፡፡

የቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት ለመከለስ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት መንግስት ለሚሰራው ስራ የላቀ ውጤታማነት ለማረጋገጥ የምክር ቤቱ ሕገ መንግስታዊ ተልዕኮ በተሟላ መወጣት መቻል ወሳኝ በመሆኑ የመንግስትን የአደረጃጀት ክለሳ ተከትሎ የቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት መሰብሰብ እና የሰው ኃይል እና ሃብቱን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህም የፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲ አሰራርና ልምዶችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከመንግስት ጋር የተናበበ የምክር ቤቱ የኮሚቴ አደረጃጀት እንዲፈጠር የሚረዳ ነው፡፡

የውሃ መስኖ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2014 ዓ.ም የቋሚ ኮሚቴው እቅድ መሰረት በክትትልና ቁጥጥር፣ በህግ አወጣጥ፣ በፓርላማ ዲፕሎማሲና በህዝብ ውክልና ስራዎች በዝግጅት ምዕራፍ በተግባር ምዕራፍና በማጠቃለያ ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራትን አካቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የአቅም ግንባታ ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ የቋሚ ኮሚቴው አባላት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ባዘጋጁት መድረክና በም/ቤቱ በተዘጋጀ ስልጠና ላይ ተሳትፈዋል እንዲሁም ከአስፈፃሚ መ/ቤት አመራሮች ጋር የትውውቅ ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡

በክትትልና ቁጥጥር ተግባራት ቋሚ ኮሚቴው የአስፈፃሚ መ/ቤቶች እቅድና አፈፃፀም ገምግሞ ግብረ-መልስ የላከ ሲሆን የከተማና የክልል መስክ ምልከታም ተካሂዷል፡፡ በከተማ መስክ ምልከታ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት ምልከታ አድርጎ አዲስ የተጀመሩ የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ መሆኑን፣ በሚ/ር መ/ቤቱና ተጠሪ ተቋማት በሰራተኞች የተነሳ የመልካም አስተዳደር ችግር መኖሩን በማየት የተገኙ ግኝቶችን አካቶ ግብረመልስ ሰጥቷል፡፡

በክልል መስክ ምልከታ በሲዳማና ደቡብ ክልሎች ምልከታ ተካሂዶ በመስክ ስራ የቡድኑ አባላት ስራቸውን ትኩረት ሰጥተው በመመልከት በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ከሚገኙ ሀይቆች

የአካባቢው ህብረተሰብ የተወሰና ተጠቃሚ ቢሆኑም እንኳን ሀይቆቹ በሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ከፍተኛ ስጋት ስር መሆናቸውን( በተለይ ሀዋሳ እጅግ በጣም እየተጎዳ መሆኑ) ፤የከተማ ንፁህ መጠጥ ውሃና ሳንቴሽን ፕሮጀክት ስራዎች በተለያዩ ምክንያቶች የተጓተቱ መሆኑ፤ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ስራዎች በተያዘለቸው ጊዜ ተጠናቀው ህብረተሰቡን ተጠቃሚ አለማድረጋቸው እና የሜትዎሮሎጂ ጣቢያ ጥራት ያለው መረጃ ለማህበረሰቡ ለማድረስ የተሻለ ስራ ውስጥ ቢሆኑም ጣቢያው በተለያዩ ቦታዎች የይዞታ መረጋገጫ ከርታ ማጣት እና የመረጃ ሰብሳቢዎች ደሞዝ ችግር እንደፈጠራባቸው የተለያ መሆኑ በምልከታው ታይቷል፡፡

በህግ አወጣጥ ተግባራት በስድስት ወሩ ለቋሚ ኮሚቴ የተመራ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ስላልነበረ የህግ አወጣጥ ተግባርን በተመለከተ የተሠራ ስራ የለም፡፡

ቅሬታና አቤቱታን ተቀብሎ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ ለቋሚ ኮሚቴው የተመራ አንድ አቤቱታ ከውሃ ፓንፕ ግዢ እና ከንብረት አያያዝ ጉድለት ጋር ተያይዞ በቀጣይ ቋሚ ኮሚቴው ከሚመለከተው አካል ጋር ተነጋግሮ ለአቤቱታ አቅራቢው ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በተመለከተ አስፈፃሚ መ/ቤቶች በእቅዳቸው ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን፣ የወጣቶችን ተጠቃሚነት እና የኤች አይቪ ኤድስ ስርጭትን ከመግታት አኳያ የሚሰሩ ስራዎች በእቅዳቸው ውስጥ መካተቱን ክትትል አድርጓል፡፡

በቋሚ ኮሚቴው በስድስት ወራት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ነበሩ በተለይ የአባላት መኖሪያ ቤትን በተመለከተ በጊዜው አለመተላለፉ አባላት ለእንግልት እንደተዳረጉና ጉዳዩን ለም/ቤቱ የማሳወቅ ስራ እንደተሰራ፣ አስፈፃሚ መ/ቤቶች እቅድና ሪፖርታቸውን ወቅቱን ጠብቀው አለመላክ የተወሰደ መፍትሄም መ/ቤቶቹ እቅድና ሪፖርታቸውን በወቅቱ እንዲልኩ የቃልና የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷ፡፡ በክልል የመስክ ምልከታ በተለይ ከግዢና ፋይናስ ዳይሬክቶሬት የአበል አሰራር ላይ ክፍተት መታየቱ እንዲሁም ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽንን በተመለከተ የካሜራማን የቪዲዮ ካሜራ ይዞ አለመቅረቡ እንደ ችግር ተወስዷል፡፡

## 1. መግቢያ

የቀድሞው የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃት የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚል ተደራጅቷል፡፡

የቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት ለመከለስ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት መንግስት ለሚሰራው ስራ የላቀ ውጤታማነት ለማረጋገጥ የምክር ቤቱ ሕገ መንግስታዊ ተልዕኮ በተሟላ መወጣት መቻል ወሳኝ በመሆኑ የመንግስትን የአደረጃጀት ክለሳ ተከትሎ የቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት መሰብሰብ እና የሰው ኃይል እና ሃብቱን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህም የፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲ አሰራርና ልምዶችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከመንግስት ጋር የተናበበ የምክር ቤቱ የኮሚቴ አደረጃጀት እንዲፈጠር የሚረዳ ነው፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕ/ተ/ም ጽ/ቤት የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተለይተው በተሰጡት የአስፈፃሚ መ/ቤቶች ላይ ተገቢውን የክትትል ቁጥጥርና ድጋፍ ሥራዎችን ለማድረግ፣ የህግ ማውጣት፣ የህዝብ ውክልናና የፓርላሜንታዊ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን በአግባቡ ለማከናወን የ2014 ዓ.ም ዝርዝር ስራ እቅድ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በበጀት አመቱ ምክር ቤቱ ከተከፈተ ጀምሮ እስከ ጥር 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

## 2. በ3 ወሩ የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራት

- የቋሚ ኮሚቴ እቅድና ቼክ ሊስት ማዘጋጀትና ለሚመለከተው መላክ፤
- የአስፈፃሚ መ/ቤቶች እቅድና ሪፖርቶችን በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት፤
- የአቅም ግንባታ መድረኮችን መሳተፍ፤
- የከተማና የክልል መስክ ምልከታ ማካሄድ፤
- የሕግ ረቂቅ አዋጅ መርምሮ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ማዘጋጀት፤
- ከህዝብና ከምርጫ ክልል የሚመጡ ጥቆማዎችን አቤቱታዎችን በመቀበል መፍታት፤

- ○ የአካባቢ ጥበቃ ስራን ሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች አካተው እንዲሰሩ ዝርዝር ቼክ ሊስት አዘጋጅቶ መላክ፤

3. <u>የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ</u>

**3.1 በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወነ**

ቋሚ ኮሚቴው የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አቅዶና አፅድቆ ለሚመለከተው አካል የላከ ሲሆን የዕቅዱ መከታተያ ቼክሊስትም ፀድቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው ስራዎችን ለማቅለል በንዑስ ኮሚቴ ደረጃ አባላትን አደራጅቶ ስራዎችን በመከፋፈል እየተከናወኑ ሲሆን ይህም ስራዎች ባለቤት እንዲኖራቸው የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

ከኮቪድ-19 ቫይረስ ጋር ተያይዞ አባላቱ ራሳቸውን እየጠበቁ እንዴት ስራ መስራት እንዳለባቸውና መመሪያን ተግባራዊ በማድረግ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

4. <u>የሰው ሀብት ልማትና አቅም ግንባታ ዘርፍ ተግባራት፡-</u>

በ3ወር ውስጥ በምክር ቤቱና አስፈፃሚ መ/ቤቶች ጥሪ እና በቋሚ ኮሚቴው አመራርና አባላት ባደረጉት መሠረት ለቋሚ ኮሚቴው የተሰጠንን የሰው ሀይል ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ማሳተፍ ተችሏል፣

**4.1 በአስፈፃሚ ተቋማት የተሰጡ ስልጠናዎች**

- ❖ የኢትዮጵያ ሜትሮዎሎጂ ኢንስቲትዩት በ10 ዓመት የልማት ዕቅድ እና ኢንስቲትዩቱ ስለሚያከናውናቸው ስራዎች ላይ ሙሉ የቋሚ ኮሚቴ አባላት ግንዛቤ አግኝቷል እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጀው የበጋ ወቅት የአየር ሁኔታ ትንቢያ መድረክ ላይ ሶስት አባላት ተሳትፈዋል፡፡
- ❖ ከጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከኢፌዴሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ባዘጋጀው የኮቪድ-19 የተሻሻሉ እና የኮቪድ መመሪያ 8/03 ማስተዋወቅን አስመልክቶ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተሳትፈዋል፡፡
- ❖ ሕግ፣ ፍትህና ዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመገናኛ ብዙሃን ባስልጣን መስሪያ ቤት በመገናኛ ብዙሀን እና የማስታወቂያ ዘርፍ ፖሊሲ፣ ሕጎችና የመገናኛ ብዙሀን ቁጥጥር ስራዎች እንዲሁም ተግዳሮቶች ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ የምክክር መድረክ ላይ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተሳትፈዋል፡፡

- "የአርብቶ አደሩ ልማት ለአገር ብልፅግና" በሚል መሪ ቃል 18ኛውን የአርብቶ አደሮች ቀን በማስመልከት የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር ባዘጋጀው መድረክ ላይ የቋሚ ኮሚቴ አባላት ተሳትፈዋል፡፡

### 4.2. ም/ቤቱ ባዘጋጀው መድረክ

- በም/ቤቱ በተዘጋጀው ስልጠና የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት፣ የፓርላማ የህግ አወጣጥ ስርዓትና የአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ፖሊሲና ስትራቴጂና እና ዋና ዋና ሴክተር ተኮር ጉዳዮች እንዲሁም  በፕላንና ልማት ሚ/ር የክትትልና ግምገማ ስርዓት ላይ የተሰጠ ስልጠና ላይ የቋሚ ኮሚቴ አባላትና ባለሙያዎች ግንዛቤ አግኝቷል ሌላው በም/ቤቱ በተዘጋጀ መድረክ ሀገር አቀፍ የህግ አውጪዎች ስልጠና ላይ አባላት ተሳትፈዋል ፡፡

### 4.3 በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ በተዘጋጀ መድረክ

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና ሚኒስቴር ድኤታዎች፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርና ሚኒስቴር ድኤታ፣ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተር፣ የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተርና ም/ዳይሬክተር፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋና ኃላፊና ም/ኃላፊዎች፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተርና ም/ዳይሬክተር እንዲሁም የየተቋማቱ የዕቅድ ዳይሬክተሮች በጽ/ቤቱ ተገኝተው ቋሚ ኮሚቴው ከላይ በተቀሰው  ሚ/ሮችና አመራሮች ጋር የትውውቅ መርሃ ግብር የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ያቀረበላቸው ሲሆን በመድረኩም የተነሱትን ሀሳቦች ቋሚ ኮሚቴው እንደግብዓት ወስዶ በቀጣይ ስራዎችን በቅንጅት ለመስራት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

**አጠቃላይ በ3ወሩ የተሳተፉ አባላት፡-**

| | | ወንድ | ሴት | አጠቃላይ የተሳተፉ አባላት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አባላት | 8 | 9 | 17 | በድግግሞሽ የተደረገ ስልጠና |
| 2. | ባለሙያ | 4 | 8 | 12 | |

4.4. **አጠቃላይ ከስልጠናው የተገኘው ውጤት፡-**

- የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የኢንስቲትዩቱ ታሪካዊ ዳራ፣ የሜትሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች፣ የኤጀንሲው መቋቋሚያ አዋጅ ላይና የሜትሮሎጂው ድርጅታዊ መዋቅርና የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ላይ በቀረቡ መድረኮች የቋሚ ኮሚቴው አባላት ሊታከሉ የሚገቡ ግብዓቶች ተነስቶ አባላትም በቀረበው እቅድ ላይ ግንዛቤ ያገኙ መሆኑን፡፡
- ም/ቤቱ ባዘጋጀው የክትትል፣ ቁጥጥርና የህግ አወጣጥ ስልትና ስርዓት ላይ አባላት ግንዛቤ ያገኙ መሆኑን፡፡
- የኮቪድ-19 የተሻሻሉ መረጃዎችና የኮቪድ-19 መመሪያ ማስተዋወቅ ላይ በቀረቡ ውይይቶች ላይ ግንዛቤ ያገኙ መሆኑ እና ስራዎች በሚሰሩበት አካባቢዎች ላይ የኮቪድ -19 ፕሮቶኮሎን ጠብቆ መከናወን እንዳለባቸው ተገንዝበዋል፡፡
- በአገሪቱ ያለውን እምቅ የተፈጥሮ ሃብት በመጠቀም የአርብቶ አደሩን ህይወት ለመቀየር እየተሰራ ያለውን ሥራ በሁሉም ክልሎች በማስቀጠል ከውጪ የሚገባ የምግብ ፍጆታን በማስቀረት የውጪ ጫናን መቀነስ እንደሚገባ በበዓሉ በተነሳው ሀሳብ ላይ ግንዛቤ አግኝተዋል፡፡

## 5. የቁጥጥርና ክትትል ስራዎች፡-

ቋሚ ኮሚቴው ሁለቱን አስፈፃሚ መ/ቤቶች /የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሁለተኛ ሩብ ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገምግሞ ግብረ-መልስ የላከ ሲሆን በጥንካሬ የተለዩት ጉዳዮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በድክመት የታዩ ጉዳዮች ደግሞ ለወደፊቱ መሻሻል እንደሚገባቸው አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

### 5.1 መስክ ምልከታ

ቋሚ ኮሚቴው በ3ወሩ ካቀደው ተግባር ውስጥ በከተማ መስክና በክልል መስክ ምልከታ ማካሄድ ሲሆን በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት መ/ቤቶችና በፕሮጀክቶች ቦታ በመገኘት የመስክ ምልከታ አካሂደዋል በዚሁ መሰረት፡-

### 5.11 የከተማ መስክ ምልከታ፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ መስክ ምልከታም ቼክ- ሊስት ተዘጋጅቶ ምልከታ የተካሄደ ሲሆን የውሃ ኢነርጂ ሚ/ርና ተጠሪ ተቋማት አዲስ የተጀመሩ የመ/ቤቱ ሪፎርምና አደረጃጀት ያሉበትን ደረጃ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት በመስክ ጉብኝት የተደረገ ሲሆን ከሠራተኞች ጋር ውይይት በማድረግ የተገኘውን ግብዓትም ከሚ/ሩና ከአመራሮች ጋር በመወያየት ቋሚ ኮሚቴው በቀጣይ መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ላይ በቃል ግብረ መልስ የተሰጠ መሆኑን እንዲሁም ለሚ/ር መስሪያ ቤቱና ተጠሪ ተቋማት የፅሁፍ ግብረ መልስ ልኳል፡፡

### 5.1.2 የክልል መስክ ምልከታ፡-

- በክልል መስክ ምልከታ በ2014 በጀት አመት በተጠሪ ተቋማት ከታቀደው ተግባር ውስጥ የፕሮጀክትና መደበኛ ስራዎች በቦታው በመገኘት የመስክ ምልከታ አካሂድዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በመደበኛ የመስክ ምልከታ ፕሮግራም በዕቅዳችን በተለየው መሠረት ከም/ቤቱ የተፈቀደውን አራት የመስክ ፕሮግራም ለይተን ለም/ቤቱ ልከናል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-
- የመጀመሪያውን ዙር የመስክ ምልከታ በሲዳማና ደቡብ ክልሎች የጊዳቦ መስኖ ልማት እና ተያያዥ ስራዎች፣ የሀዋሳ ከተማ ንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን፣ የካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት፣ የአዋሳ ኃይቅና አካባቢ ጥበቃ ስራዎች የአባያና ጫሞ ኃይቆች እንክብካቤ ስራዎችና፣ የሀዋሳ ሜትሮሎጂ ጣቢያ ስራዎችን ለመመልከት ሦስት አባላትና አንድ ባለሙያ ቼክ ሊሰት አዘጋጅተው በቋሚ ኮሚቴ ከፀደቀ በኃላ በም/ቤቱ በተፈቀደ ፕሮግራም መሠረት ምልከታውን አከናውኗል፡፡ በዚሁ መሠረት ቋሚ ኮሚቴውም የመስክ ምልከታው ሪፖርት ከገመገመ በኃላ ለሚመለከተው አካል ልኳል፡፡

## 6. <u>ያልተከናወኑ ተግባራት</u>

→ በክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ላይ ሌላው የቋሚ ኮሚቴ ተግባር የአስፈፃሚ መስሪያ መ/ቤቶችን እቅድና አፈፃፀም መከታተል መቆጣጠር ነዉ፡፡ ነገር ግን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት እቅድ አቅዶ ያላከ ስለሆነና እንዲሁም የአንደኛና ሁለተኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም ዘግይተው በመላካቸው ግብረ-

መልስ አልተሰጠም በቀጣይ መስተካከል እንደሚገባው በቃልና በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡

→ ህግ አወጣጥ በተመለከተ ቋሚ ኮሚቴውን የሚመለከት ረቂቅ አዋጅ ስላልተመራ አልተከናወነም፡፡

7. **ከህዝብና ከምርጫ ክልል የሚመጡ ቅሬታና ጥቆማዎችን በመቀበል የመፍታት ሂደትን በተመለከተ፣**

- በቋሚ ኮሚቴው በ3ወር ውስጥ  የተመራ አንድ አቤቱታ ከውሃ ፓንፕ ግዢ እና ከንብረት አያያዝ ጉድለት ጋር ተያይዞ አቤቱታ ቀርቧል፡፡ በቀጣይ  ቋሚ ኮሚቴው ከሚመለከተው አካል ጋር ተነጋግሮ ለአቤቱታ አቅራቢው ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን፡፡

8. **<u>የአመራርና አባላት ሁኔታን በተመለከተ፣</u>**

በሦስት ወራት ውስጥ ዕቅድ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ በቋሚ ኮሚቴአችን አባላት የነበሩ እንቅስቃሴ በተመለከተ፣

**<u>በቋሚ ኮሚቴው ጥንካሬ ላይ የታዩ ጉዳዮች</u>**

- ቋሚ ኮሚቴው የሚሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ መፈፀም መቻሉ
- አባላት በቡድን መንፈስ በመግባባትና በመተካካት ተሳትፎ ማድረጋቸው
- ለስራው ያላቸው ተነሳሽነትና ቅልጥፍና

**<u>በቋሚ ኮሚቴው ድክመት ላይ የታዩ ጉዳዮች</u>**

- አንዳንድ አባላት በተለያዩ ምክንያቶች ስብሰባ ላይ አለመገኘት  ፡፡

9. **<u>የባለብዙ ዘርፍ ሥራዎች</u>**

- የክትትልና ቁጥጥር መተግበሪያ ቼክ ሊስት የዘርፈ ብዙ ስራዎች ላይ ቋሚ ኮሚቴው ሪፖርትና ዕቅድ በሚገመግምበት፣ መስክ ምልከታ በሚያደርግበት ወቅት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለይቶ ሁሉም አስፈፃሚ መ/ቤቶች አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችና አረንጓዴ ልማትን በዕቅዳቸው ውስጥ አካተው እንዲሰሩ ለሁሉም ቋሚ ኮሚቴ  ቼክ-ሊስቱን አዘጋጅቶ የላከ መሆኑን፡፡
- አስፈፃሚ ተቋማት ለቋሚ ኮሚቴ በሚያዘጋጀው መድረክ ላይ የቋሚ ኮሚቴ የሴቶችን  ተሳትፎ እንዲጠናከሩ ሴቶችንና አሳታፊ ያደረጉ መሆኑንና ቋሚ ኮሚቴው ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት በሚገመግምጉበትና  የመስክ ምልከታ

በሚያካሂዱበት ወቅት የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞችን የአካባቢ ጥበቃ ስራዎችን አካተው መስራታቸውን ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን፡፡

10. <u>*ያጋጠሙ ችግሮች፡*</u>

- የአባላት መኖሪያ ቤትን በተመለከተ ቤት ያልተሰጣቸው ሁለት/2/ አባላት እንዳሉና በጊዜው ተጠናቆ አለመተላለፉ አባላትን ለአላስፈላጊ እንግልት እየዳረገ መሆኑ፡፡
- አስፈጻሚ መ/ቤቶች እቅድና አፈፃፀም ወቀወቱን ጠብቀው አለመላክ
- የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በመኖሩ ምክንያት ለስራ ምቹ ሁኔታ አለመፈጠሩ፣ **ለአብነት**፡- የማስክ፣ የሳኒታይዘር አቅርቦት አለመኖር፤
- የቋሚ ኮሚቴው አባላት ስራዎችን ለማቅለል በንዑስ ኮሚቴ ደረጃ የተደራጁ ሲሆን ይህም ስራዎች ባለቤት እንዲኖራቸው የራሱን አስተዋፅኦ ያበረከተ ቢሆንም ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለንዑስ ኮሚቴ አባላት ስራዎችን በተቀላጠፈ መንገድ ለማከናወን የቢሮ ጥበት ችግር እንዳለ ተስተውሏል፡፡
- በከተማ መስክ ምልከታ የሚዲያ ሽፋን አለመገኘት ለአብነት፡- የውሃና ኢነርጂ ሚ/ርና በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት፤
- በመደበኛ /ክልል/ መስክ ምልከታ ላይ ብዙ ችግሮች ያጋጠሙ ሲሆን **ለአብነት** በጣም ዝቅተኛ የውሎ አበል ክፍያ፣ የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ እጅግ በጣም ችግር የፈጠረ መሆኑን፤
- የምክር ቤቱ የስብሰባ ፕሮግራም መዛባት ስራችን ላይ እንቅፋት ፈጥሯል ለአብነት፡- በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር በቋ/ኮ እቅድ መሰረት ምልከታ ለማድረግ ተፈልጎ ምልከታው በሚደረግበት ቀን የም/ቤት ስብሰባ አለ መባሉ ለስራው መስተጓጎል ምክንያት ሆኗል
- የተወሰኑ አባለት ባልታወቀ ምክንያት ከስራ መቅረታቸው፤
- አንድ የቋሚ ኮሚቴ አባል ወደ ፕላንና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተዘዋወሩ መሆኑንና በምትኩ ሌላ አባል አለመተካቱ፤

11. <u>የተወሰዱ መፍትሔዎች፡-</u>

- የአባላት መኖሪያ ቤት ጉዳይን በተመለከተ ለጽ/ቤቱ የአስተዳደራዊ ጉዳዮች ዘርፍ በማሳወቅ መኖሪያ ቤቱ በፍጥነት ተጠናቆ ለአባላት እንዲተላለፍ ተጠይቋል፡፡
- አስፈፃሚ መ/ቤቶች እቅድና አፈጻፀማቸውን ወቅቱን ጠብቀው እንዲልኩ የቃልና የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል
- የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን በተመለከተ የኮቪድ መመሪያን ተግባራዊ በማድረግ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡
- ለንዑስ ኮሚቴ ስራ መሳካት ዋናውን የመሰብሰቢያ አዳራሽና የአመራሮች ቢሮን በመጠቀም ስራዎች ተከናውነዋል፡፡
- የቋሚ ኮሚቴ ስራዎች የሚዲያ ሽፋን አለማግኘት ለም/ቤቱ የሚዲያና ኮሚኒኬሽን ዘርፍ ያሳወቀ መሆኑ፡፡
- የውሎ አበልና በጣም ዝቅተኛ መሆኑና የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ችግርን ም/ቤቱ መፍታት አለበት፡፡
- የቋሚ ኮሚቴው አባላት በተስማሙበት መሰረት የመስክ ምልከታውን ለሌላ ጊዜ በማስተላለፍ ለም/ቤቱ ስብሰባ ቅድሚያ ተሰጥቷል፡፡

12. <u>የሚቀጥለው ወራት የትኩረት አቅጣጫ</u>

- በመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት በመገኘት የመስክ ምልከታ በማድረግ ከማኔጅመንቱና ከሰራተኛው ጋር መወያየት፤
- በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት በመገኘት የመስክ ምልከታ በማድረግ ከማኔጅመንቱና ከሰራተኛው ጋር መወያይት፤
- በታላቁ ህዳሴ ግድብ ብሔራዊ ማስተባሪያ ም/ቤት ፅ/ቤት በመገኘት የመስክ ምልከታ በማድረግ ከማኔጅመንቱና ከሰራተኛው ጋር መወያይት፤
- የሁለተኛ ዙር የክልል የመስክ ምልከታ ማካሄድ ቼክ ሊስት ማዘጋጀት፤
- ሚያዚያ 4 2014 ዓ.ም አስፈፃሚ መ/ቤቶች ም/ቤት በመቅረብ የዘጠኝ ወራት አፈፃፀም ስለሚያቀርቡ ጥያቄ ማዘጋጀት፤

## 13. ማጠቃለያ

የቋሚ ኮሚቴው ያለፉትን ሦስት ወራት ዕቅድ አፈፃፀማችን ከላይ በዝርዝር በተገለፀው መሠረት የተፈፀመ መሆኑና በቀጣይ ቀሪ ወራት በዕቅዳችንና ቼክሊስት መሠረት እየተመራን የክትትልና ቁጥጥር ሥራችንን በአግባቡ በመፈፀም የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መንገድ ተጠናክረን ተልዕኳአችንን በብቃት መፈፀም ይኖርብናል።

# የኮሚቴ አባላት የስብሰባ ተሳትፎ

| ተ.ቁ | ቋሚ ኮሚቴ | የቋሚ ኮሚቴው አባላት ብዛት | በቋሚ ኮሚቴው የካሄደ ስብሰባ ብዛት | በስብሰባ ላይ የተገኙ አባላት | በስብሰባ ላይ ያልተገኙ አባላት | አባላት ያልተገኙበት ምክንያት | | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በፍቃድ | በሥራ | በህመም | ያለፈቃድ | ድምር | |
| | የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት | 12 | 11 | | | | | | | | |
| 1. | የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲያ አህመድ | -- | - | - | - | - | - | - | - | - | |
| 2. | የተከበሩ አቶ አወቀ አምዛዬ/ዶ/ር | | | | 1 | - | √ | - | - | - | |
| 3. | የተከበሩ አቶ እሱባለው መብራት | | | | 1 | - | √ | - | - | - | |
| 4. | የተከበሩ አቶ መስፍን ዳኜ | | | | 2 | √ | √ | - | - | - | |
| 5. | የተከበሩ አቶ ዓለሙ ጌታሁን | | | | 2 | √ | √ | - | - | - | |
| 6. | የተከበሩ አቶ ኢብሳ ዩሱፍ | | | | 7 | √ | - | - | - | - | |
| 7. | የተከበሩ አቶ አሜ አብደላ | | | | 6 | - | - | √ | - | - | |
| 8. | የተከበሩ ወ/ሮ አበባ ሳዲቅ | | | | 1 | - | √ | - | - | - | |
| 9. | የተከበሩ ወ/ሮ ነጋሴ ባይሳ | | | | 1 | - | √ | - | - | - | |
| 10. | የተከበሩ አቶ ካሳሁን ጆቢር | | | | 10 | √ | - | - | - | - | |
| 11. | የተከበሩ አቶ አብዲላሂ መሀመድ | | | | 11 | √ | - | - | - | - | |
| 12. | የተከበሩ ወ/ሮ ሀስናን ሀንፍሬ | | | | 10 | √ | - | - | - | - | |